የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN COMMUNICATIONS AUTHORITY

# የሞባይል ቁጥር ማዛወር መሚያ ማዘራሪያ ጽሁፍ

## 1. መግቢያ

የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥሮች ውስን የሃገር ሀብቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም እነዚህን የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥሮች ውጤታማ ምደባ፣ አጠቃቀም እና አስተዳደር ያስፈልጋቸዋል፡፡ በሚሆኑም ቁጥሮች ከአንድ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ወደ ሌላ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር የሚዛዋሩበት መንገድ እና ከእዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሞባይል ተጠቃሚዎች መብቶችን በተመለከተ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የአሰራር ስርሃትን ማዘርጋት ተገቢ ነው፡፡

ከዚህም ባለፈ የሞባይል ቁጥሮች ዝውውር የደንበኞችን ፍላጎት እና መብት እንዳይገድብ ተገቢ የሆነ ክትትል ሚድረግ የሚያስፈልግ ሲሆን ለዚህና ከላይ የተመለከቱ ጉዳዮችን ተፈጻሚ ለሚድረግ ዘርፉን የሚያስተዳድር የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

ይህን መሰረት በሚድረግ ባለስልጣኑ የሞባይል ቁጥር ዝውውር መመሪያ ያዘጋጀ ሲሆን ይህም ዘርፉን በአግባቡ ማስተዳደር የሚያስችል ድንጋጌዎች የያዘ እና ውጤታማ ስራን መስራት ያስችላል ተብሎ ይታመናል።

## 2. የመመሪያው የሕግ መሰረት

የኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን ባለሥልጣን በኮሚኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 አንቀጽ 28 (4) እና 54(2) መሰረት የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥር ዝውውር መመሪያ ማውጣት እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች ላይ ባለስልጣኑ ደንበኞች የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥሮቻቸውን ሳይቀይሩ ከአንድ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ወደ ሌላ ኦፕሬተር ማዛወር የሚችሉበትን የአሰራር ስርሃት በተመለከተ መመሪያ የማውጣ ስልጣን እንደተሰጠው በግልጽ ተመልክቷል። ከዚህ በተጨማሪም ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 54(2) መሠረት አዋጁን እና አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦችን የሚከፈጸሚያ መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን የተሰጠው ሲሆን እነዚህን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት በሚድረግ ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## 3. የመመሪያው ዓላማ

ይህ መመሪያ የተለያዩ አላማዎችን ከግብ ለሚድረስ የተዘጋጀ ሲሆን በዚህ ክፍል ዋና ዋና ሊባሉ የሚችሉ የመመሪያውን አላማዎች ተመልክተዋል፤ -

- በቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል የሚደረገውን የሞባይል ቁጥር የማስተላለፍ ሂደት ፍትሃዊ፣ ከብክነት የጸዳ እና ውጤታማ ሚድረግ፣
- የሞባይል ቁጥሮች ዝውውር የሚተዳደርበት ስኬታማ የሞባይል ቁጥሮች ዝውውር የህግ ማእቀፍ ማበጀት፣

- ተጠቃሚዎች የግል ሞባይል ቁጥር፣ የቢዝነስ ስልክ ቁጥር፣ የጋራ ቁጥር እንዲሁም ሌሎች ቁጥሮችን ወይም ቀድሞ የነበረን አገልግሎት መቀየር ሳያስፈልግ ከአንዱ ኦፕሬተር ወደ ሌላኛው ኦፕሬተር ማሻጋገር የማቻሉበትን ሁኔታ በመፍጠር የተጠቃሚዎችን እርካታ ማረጋገጥ፤

## 4. የመመሪያው የዝግጅት ሂደት

የመመሪያው ዝግጅት ከአንድ አመት በላይ የወሰደ እና በርካታ ሂደቶችም ያለፈ ሲሆን ረቂቅ ህጉ ተጠናቅቆ እስከቀረበበት ድረስ የተከናወኑ አበይት ተግባራት ወይም ሂደቶች በሚከተለው ሜልኩ ተጠቃልሏል።

- **ጥናት ማካሄድ፡-** እስካሁን ድረስ በሃገሪቱ ወስጥ የሞባይል ቁጥሮች ዝወውርን የተማለከተ ዘርፍ ተኮር ህግ የለም፡ በመሆኑም ዘርፉን ማሰረት ያደረገ ህግ ለመቅረጽ ጥናቶች ማካሄድና የሌሎች ሃገራትን ልምድ ሚዳት የሚጠይቅ ነው፡ ይህንን ለማካካት የሃገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ እና በዘርፉ የዳበረ ልምድ ያላቸው የሃገራት ተሞክሮ ላይ  ጥናት ተደርጎል። በዚህ ጥናት አማካኝነትም በመሚያ ወስጥ ሊካተቱ የሚባቸው ድንጋጌዎቸ እና ዋና ዋና ቁም ነገሮች ተለይተዋል።
- **ለረቂቅ ህጉ ዝግጅት ግብአት የሚሆኑ ሞዴል ህጎችና ተሞክሮዎች ማምረጥ፡-** የቴሌኮም ዘርፍ ላይ አለም–አቀፍ ተቋማት ተሳታፊ በሚሆናቸው ዘርፉን የሚያስተዳድረው ህግም አለምአቀፍ ደረጃወን በጠበቀ ሜልኩ ማዘጋጀት አለበት። ስለሆነም የህጉ ይዘት አለም አቀፍ ደረጃው የጠበቀ ይሆን ዘንድ ከሃገሪቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች አንጻር ተቀራራቢ የሆኑ ሃገራት ህጎች በሞዴልነት ተመርጠዋል።
- **ባለድርሻ አካላትን ማወያየት፡-** ረቂቅ መመሪያወን ለማዳበር የሚከተሉት ሶስት የወይይት መድረኮች ተዘጋጅተዋል፡-
    - የሃገር ወስጥ እንዲሁም አለማቀፍ የቴሌኮም ኦፕሬተሮችን፣ ከዘርፉ ጋር ግንኙነት ያላቸው የመንግስት እና የግል ባለድርሻ አካላትን፣ የሲቪክ ማህበረሰብን፣ ዘርፉ ላይ የሚሰሩ የህግ ባለሞያዎችን ፣ባለሃብቶችን ወዘተ ተሳታፊ ያደረገ የአንድ ወር የምክከር መድረክ ተዘጋጅቷል።
    - ረቂቁን በባለስልጣኑ ዌብሳይት ላይ ለ20 ቀናት ለሕዝብ አሰተያየት ክፍት እንዲሆን ተደርጎ፤ ፍላጎቱ ካላቸው የሃገር ወስጥ እንዲሁም አለምአቀፍ ተቋማት በቂ የሆነ ግባት ለማሰብሰብ ተችሏል።
    - ባለድርሻ አካላት ያነሱት ነጥቦችን እና ባለስልጣኑ የሰጠወን ምላሽ በተማለከተ ሦስተኛ የምክክር መድረክ ተዘጋጅቷል። በዚህ መድረክ ላይ በተሳታፊዎች የተነሱ ነጥቦች ላይ ወይይት የተደረገ ሲሆን በመመሪያው ላይ ሊካተቱ የሚገቡ ተጨማሪ ግባቶች ተገኝተዋል።

## 5. በረቂቅ መመሪያው ላይ የተነሱ ነጥቦች እና የተወሰዱ እርምጃዎች

በረቂቅ መመሪያው ላይ የተለያዩ የሃገር ወስጥ እና የወጪ ሃገር ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ የሆኑ ሲሆን በሜድረኩ ላይ የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስተዋል። ከነዚህም ወስጥ የሚከተሉት ዋና ዋና ናቸው።

- በአዋጁ የተሰጡ ስልጣኖች እንደተጠበቁ ሆነው በመግቢያ (preamble) ክፍል ላይ መመሪያውን ማውጣት ያስፈለገበት ዋና ምክንያቶች ተለይተው በአንድ ወይም ሁለት ፓራግራፍ ወስጥ እንዲካተት ቢደረግ፤
- የክፍል አንድ ርዕስ ዝርዝሮቹን በማስወጣት "ጠቅላላ" ብቻ በሚል እንዲስተካከል ቢደረግ፤
- በረቂቅ መመሪያው ላይ የቃላት አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ ቢደረግ፤
- የቁጥር ዝወመር ስራን (NPC)ከባለስልጣኑ ወጪ ያለ የንግድ ተቋም እንዲያከናወነው ቢደረግ፤
- የቁጥር ዝወመር ስራን(NPC) የሚያከናወነው ሌላ ተቋም ከሆነ፤ ባለስልጣኑ ከዚህ ጋር የተያያዘ አገልግሎት ማስጫ ደስክ መመስረት አይጠበቅበትም፡
- የቁጥር ዝወመር መጀመሪያ ቀናቶች በመመሪያው ላይ ባይገለጹ፤
- መመሪያውን ማሻሻል በተመለከተ ክፍል ላይ መመሪያው በማንኛውም ወቅት እንደሚሻሻል ተደንግጓል። ይህ ግን የባለፍቃዶችን ጥቅም ስለሚጎዳ ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ቢፈጠር።

ከላይ የተመለከቱት እና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎች ላይ ሰፊ ወይይት የተደረገ ሲሆን ባለስልጣኑም የሃገሪቱን ጥቅም እና የቴክኖሎጂውን ማስፋፋት የሚያረወን ፋይዳ ግንዛቤ ወስጥ በማካትት የሚከተሉት ወሳኔዎች ተወስነዋል፡-

- የመመሪያው ርዕስ ላይ የተነሳው ጥያቄ አግባብነት ስላለው ማሻሻያ ተደርጎበታል፤
- መግቢያው ላይ የተነሳው ጥያቄ አግባብነት ያለው በመሆኑ ማሻሻያ ተደርጓበታል።
- ክፍል አንድ አወቃቀር ላይ የተነሳው ሐሳብ ተገቢነት ስላለው ማሻሻያ ተደርጎበታል፤
- በረቂቅ መመሪያው ላይ የቃላት አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ ቢደረግ የሚለው ነጥብ ተገቢነት ስላለው ማሻሻያ ተደርጎበታል፤
- የቁጥር ዝወመር ስራን ከባለስልጣኑ ወጪ ያለ የንግድ ተቋም ቢያከናወነው የተሻለ ነው የሚለው ነጥብ ተገቢነት ስላለው አደረጃጀቱ በዛ መልክ እንዲሆን ተደርጓል፤
- የቁጥር ዝወመር ስራን የሚያከናወነው ሌላ ተቋም ከሆነ፤ ባለስልጣኑ ከዚህ ጋር የተያያዘ አገልግሎት ማስጫ ደስክ መመስረት አይጠበቅበትም የሚለው ነጥብ ተገቢ በመሆኑ ተገቢው ማስተካከያ እነዲደረግበት ተደርጓል፤
- የቁጥር ዝወመር መጀመሪያ ቀናቶች በመመሪያው ላይ ባይገለጹ የሚለው ሃሳብ ተገቢነት ስላለው ማሻሻያ ተደርጎበታል፤
- መመሪያውን ባለስልጣኑ በማንኛውም ወቅት እንደሚያሻሽለው የተመለከተው ንግግር የአገልግሎት ሰጪዎችን ፍላጎት ስለሚጎዳ ይሻሻል የሚለው ጥያቄ ተገቢነት ስላለው ማሻሻያ ተደርጎበታል።

በዚህም ማስረት ባለሰልጣኑ መመሪያወን ከማሻሻሉ በፊት ከባለድርሻ አካላት ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ወይይት ማድረግ እንደሚኖርበት ተመልክቷል።

**6. ለወይይት የተሰራጨው ረቂቅ መመሪያ እና የሚጨረሻ ሆኖ የወጣው መመሪያ**

- በመመሪያው መግቢያ ላይ ለመመሪያው ማሰረት የተደረጉ ድንጋጌዎች ብቻ ናቸው የተካተቱት። ለመመሪያው መውጣት ምክንያት የሆኑ ነጥቦች አልተካተቱም የሚል አስተያት ከባለደርሻ አካላት በኩል ቀርቧል። ስለሆነም የመመሪያው መግቢያ የመመሪያወን አስፈላጊነት አጉልቶ በሚያሳይ ሚልኩ በድጋሚ ይስተካካል የሚለው ሐሳቤ/ አስተያት ተገቢ በማሆኑ በዛ ሚልክ እንዲስተካከል ተደርጓል።

- ክፍል አንድ የተዋቀረበት መንገድ የሃገሪቱን የህግ አወቃቀር የተከተለ አይደለም የሚለወን ጥያቄ በመቀበል በሃገሪቱ የተለመዱ የህግ አወቃቀር ተፈጻሚ እንዲሆን ተደርጎል፤

- በረቂቅ መመሪያው ላይ የቃላት አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ ቢደረግ የሚለው ነጥብ ተገቢነት ስላለው ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡ ይህንም ማሰረት በማድረግ በአማርኛወም ሆነ በእግሊዘኛው መመሪያ ላይ የማገኙ ቃላቶች ተገቢ ማስተካካያ ተከናወኖባቸዋል፡፡

- የቁጥር ዝወዉር ስራ ከባለስልጣኑ ወጪ ያለ የንግድ ተቋም ቢያከናወነው የተሻለ ነው የሚለው ነጥብ ተገቢነት ስላለው አደረጃጀቱ በዛ ሚልክ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በዚህም ባለስልጣኑ ይህን ስራ ለሌላ ሶስተኛ ወገን እንዲሰራ ፈቃድ ሊሰጥ እንደሚቻል ተመልክቷል፡፡

- የቁጥር ዝወዉር ስራ የሚያከናወነው ሌላ ተቋም ከሆነ፤ ባለስልጣኑ ከዚህ ጋር የተያያዘ አገልግልግሎት ማሰጫ ደስክ መማሰረት አይጠበቅበትም የሚለው ነጥብ ተገቢ በማሆኑ ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግበት ተደርጓል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ባለስልጣ ክትትል የሚያደርግ ወይም ማሰል ስራን የሚሰራ አደረጃጀት የሚዜጠር ይሆናል፡፡

- የቁጥር ዝወዉር መጀመሪያ ቀናቶች በመመሪያው ላይ ባይገለጹ የሚለው ሃሳብ ተገቢነት ስላለው ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡

- በማስታወቂያ በተሰራጨው መመሪያ ላይ ባለስልጣኑ መመሪያወን በማንኛወም ወቅት እንደሚያሻሽለው ተመልክቷ የነበረ ሲሆን በሚጨረሻ ረቂቅ ላይ ግን ባለስልጣኑ መመሪያወን ሲያሻሽል ከባለድርሻ አካላት ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ወይይት ማድረግ እንደሚኖርበት ተመልክቷል። ይህ የተደረገበት ዋና ምክንያት ባለስልጣኑ በየወቅቱ ባለድርሻ አካላትን ሳያሳትፍ ማሻሻያ የሚያደርግ ከሆነ የአገልግሎት ሰጪዎችን ፍላጎት/ጥቅም ይጎዳል ከሚል ሐሳቤ የተነሳ ሲሆን ይህም ከባለድርሻ አካላትም በኩል በስፋት ሲንጸባረቅ ነበር። ጥያቄው የአዋጁን መንፈስ ያገናዘበ እና ተገቢ በማሆኑ እንዲስተካከል ተደርጓል።